# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(አንድነት/United)


ጥቅምት 26 ቀን 2010 ዓ. ም
November 5, 2017

## የጎሣ ፖለቲካና መዘዙ

የህወሓት አገዛዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደበፊቱ ረግጦ ለመግዛት ከማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን በማወቁ በተጠናወተው በሥልጣን ላይ የመቆየት ፍላጎቱ ሕዝብን ከሕዝብ፣ ብሔረሰቦችን ከብሔረሰቦች ማጋጨቱን በሰፊው ተያይዞታል። ይህ አዲስ ስልቱ ባይሆንም፣ የአሁኑን ከቀድሞዎቹ እኩይ ተግባሮቹ የሚለየው፣ በበርካታ አካባቢዎች በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ሰለባ ማድረጉ ነው። ቀውሱን እራሱ የፈጠረው ቢሆንም ሌላው ቢቀር፣ ቀውስ በተፈጠረባቸው አካባቢዎች በፍጥነት በመድረስ፣ ሕዝብን ማረጋጋትና ምርመራ በማድረግ ውጤቱን ለሕዝብ ማስታወቅና ለወደፊት ችግሩ እንዳይደገምም መከላከያ መንገዶችን ማዘጋጀት ይጠበቅበት ነበር። ይሁን እንጂ የህወሓት ሥነ-ባህሪ ሕዝብን መታደግ አይደለምና ይህን ያደርጋል ብለን አንጠብቅም።

ህወሓት ምን ገደደውና?

ከመጋቢት 2009 ጀምሮ በአዋሳኝ ቦታዎች በሚገኙ ኦሮሞዎችና ኢትዮጵያውያን ሶማሌዎች መካከል በተቀሰቀሰው ግጭት ከሁለቱም ወገኖች በመቶ ሺዎች የሚገመቱ ወገኖቻችን ከመኖሪያ ቦታቸው ተፈናቅለው በመጠለያ ጣቢያዎችና በከተሞች ውስጥ በስቃይ ይኖራሉ። በጥገኝነት በጎረቤት ሀገር በሶማሊላንድ የሚኖሩ ኦሮሞዎችም በአሰቃቂ ሁኔታ ከሚኖሩበት ሰላማዊ የስደት ኑሮ ተፈናቅለው በእንግልት ላይ ይገኛሉ። ችግሩ በዋናነት በተከሰተባቸው አወዳይን በመሳሰሉ አካባቢዎች ደግሞ የሟቾች ቁጥር በመቶዎች እንደሆነ ይነገራል። እስካሁን ያሉ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ የችግሩ መንስዔ የህወሓት አገዛዝ ከኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ልዩ ኃይል ጋር በሚስጥር በመተባበር ባደረገው ተንኮል እንደሆነ ይነገራል። ጉዳዩ ሙሉ በሙሉ ተአማኒነት ባለው መልኩ የሚረጋገጠው ግን ከህወሓት ነፃ የሆነ መርማሪ ኮሚሽን ይህንንና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮችን ሁሉ መርምሮ፣ ለሕዝባችን ሲያቀርብ ብቻ


P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009
Phone: 202- 241 2078
Email Address: eprp-united@eprp-ihapa.com

ነው። በተመሳሳይ ወቅት በአፋር ልዩ ኃይልና በራያ ዜጎች መካከል ረዥም ሰዓታት የፈጀ ጦርነትም ተካሂዷል።

ሕዝባችን ከዚህ ችግርና ቀውስ ሳያገግም፣ ሌላ የግጭት ማዕበል ደግሞ በኢሉባቦር ቀጠና በጥቅምት ወር 2010 ተከሰተ። በቡኖ በደሌ ቢያንስ በአምስት ወረዳዎች ውስጥ ኗሪ በሆኑ አማሮች ላይ ያነጣጠረ የሰው ሕይወት እልቂት፣ የንብረት ዝርፊያና ቃጠሎ በሰፊው በመካሄዱ፣ ተጠቂዎቹ ሕይወታቸውን ለማዳን ወደጫካ እንዲሸሹ ተገደዋል። እስካሁን የሞቱት ሰዎች ቁጥር ከ20 በታች ነው ተብሎ ቢገመትና ከሟቾች መካከል አማሮችም ኦሮሞዎችም ይገኛሉ ቢባም ጉዳዩ በጥልቅና በነፃ መንገድ ቢመረመር ምናልባት ከዚህ የከፋ ሊሆን ይችላል። በአማራ ወገኖቻችን ላይ ይህ ዓይነት ጥቃት ሲደርስ ይህ የመጀመሪያው እንዳልሆነ ሕዝባችን ያውቀዋል።

የህወሓት የዘር ፖለቲካና ፌደሬሽን ተብየው በተግባር ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ፣ ባመዛኙ የቅድሚያ ሰለባ የሆኑት በተለያዩ የደቡብና የምሥራቅ የአገራችን ክፍሎች የሚገኙት የአማራ ተወላጆች ነበሩ። አስቃቂው ድርጊት በኦሮሞ ተወላጅ ስም በህወሓት ተመልምለው የገቡ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨት የተሰለፉ ግለሰቦች ለመሆናቸው ልዩ ልዩ ተጨባጭ መረጃዎች እያመላከቱ ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ግን አማሮችን ከጥቃት ለማዳን ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ለመሆኑ የአማራ ተወላጆች በመገናኛ ብዙሃን ገለጸዋል።

በኢሉባቦር ሰለባ የሆኑ አማሮች በ1977 በዘመነ-ደርግ በተከሰተው ረሀብ በድርቅ ከተጎዱት የአገራችን ሰሜናዊ ክፍሎች ደቡብ የሠፈሩ ዜጎችና ባለፉት 33 ዓመታት እዚያው ተወልደው የኖሩ፣ ወልደውና ከብደው የሚኖሩ ዜጎቻችን ናቸው። የኦሮሞና የአማራ የአገር ሽማግሌዎች እንደሚሉት፣ እንደዚህ ዓይነት ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጭ ድርጊት በአካባቢያቸው ፈጽሞ ያልታየ አዲስ ክስተት እንደሆነ ነው።

ኢሕአፓ (አንድነት) እንደሌሎች ድርጅቶች፣ ተቋማትና ግለሰቦች፣ በምንም መልኩ የሚከሰትን የዘር ፖለቲካን መጥፎ ገጽታ ከማሳየት ቦዝኖ አያውቅም። ይሁንና ሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመምጣቱ እነሆ ዛሬ የዘር ፖለቲካ ቤቱን ያላንኳኳበት፣ ከብሂረሰቡ የሕይወት ወይም የንብረት ጥፋት ያልደረሰበት፣ በሥነልቦና ጥቃትና ስጋት ያልቆሰለበት ኢትዮጵያዊ ወገን

የለም መናገር ይቻላል። በዘር ፖለቲካ ተመሥርተው አስተዳደሩን አጨማልቀው የቆዩ የኢህአዴግ ጥምር ድርጅቶች አባላት ዛሬ በእርስ በርስ የሥልጣን ሽሚያ፣ አንዱ አንዱን ጠልፎ ለመጣል በሚያደርጉት ሽኩቻ፣ በተለይም አለቃቸው ህወሓት ተቀናቃኞቹን ለማሳነስና የመሪ ቦታውን ይዞ ለመቆየት ሕዝብን ከሕዝብ በማጋጨት እኩይ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ከምን ጊዜውም በበለጠ ተግቶ እየሠራ መሆኑም ይስተዋላል።

እነዚህ ኃላፊነት የጎደላቸው የአገዛዙ ወንጀለኞች የሚያደርሱትን ጉዳት ሊመክቱ ከሚችሉ ኃይሎች ውስጥ የአገር ሽማግሌዎች ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ ብለን እናምናለን። በየአካባቢ የሚኖሩ ሽማግሌዎች የአገዛዙን ተንኮል ተረድተው ቀውስ በተፈጠረባቸው ቦታዎች ሁሉ የአስታራቂነትና ወንጀለኞችን የመለየት ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ኢሕአፓ (አንድነት) አደራ ይላል። ቀውሱ ባልደረሰባቸው ቦታዎችም ቢሆን ሽማግሌዎች ከወዲሁ ነቅተው በመጠበቅ ሕዝብን ከሕዝብ ማቀራረብና በተለይ ወጣቶችን መምከር ይጠበቅባቸዋል። ምንም እንኳን ፀረ-ህወሓት ዴሞክራሲያዊ ሰልፎች የተራማጅነት ሚና ቢኖራቸውም፣ ህወሓት እነዚህን ሰልፎች ወደ ብሄረሰብ ግጭት ስለሚለውጣቸው፣ ሕዝባችን ነቅቶ ፀረ-ህወሓት እንቅስቃሴው ወደ እርሰ በርስ ግጭት እንዳይቀየር በማድረግ የነገዋን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረግ ይችላል።

ከዚህ ደረጃ ለመድረስም የተቃዋሚ ኃይሎች አስተዋጽዖ በእጅጉ ወሳኝ በመሆኑ፣ ልዩነታቸውን በማቻቻል በአንድነትና በኅብረት ቆመው ይህን አገር አጥፊ የህወሓት አገዛዝ ሊያስወግዱ ይገባቸዋል። የሁሉም ዜጎች መብቶች ሙሉ ለሙሉ ሊከበሩ የሚችሉት በኢትዮጵያዊነት የዜግት ክብር ብቻ ነውና። ስለሆነም ኢሕአፓ (አንድነት) ዘወትር እንደሚያሳስበው ዛሬም በተደጋጋሚ አብረን በኅብረት፣ በአንድነት እንሥራ የሚል ጥሪውን ለተቃዋምክ ኃይሎች ሁሉ ያስተላልፋል።

ኢሕአፓ (አንድነት) በሐረር፣ በኢሉባቡር፣ በአምቦ፣ በጎንደር፣ በጎጃም፣ በወሎና በሌሎችም አካባቢዎች በሞቱት ወገኖቻችን ምክንያት የተሰማውን ጥልቅ ኃዘን እየገለጸ ለቤተሰቦቻቸው ሁሉ መጽናናቱን እንዲሰጣቸው ይመኛል።

ሞት ለዘር ፖለቲካ!!

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address**: eprp-united@eprp-ihapa.com